# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 32 ኛ ሳምንት
## ለሐዋርያነት የተመረጠው ማትያስ

**ዓላማ**

- ማትያስ ለሐዋርያነት ስለ መመረጡና ስለ በዓለ ጰራቅሊጦስ መማር።

**ምንባብ**

- የሐዋ. 1÷15-26

**መግቢያ**

- ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፣120 የክርስቶስ ቤተሰቦች በቤት ተሰብስበው ይጸልዩ ነበር፤ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 12 ደቀመዛሙርት ነበሩት ከእነርሱ አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ ጌታችንን ካደ።
- በዛሬው ትምህርታችን በይሁዳ ምትክ ሐዋርያ እንዲሆን የተመረጠውን አባት አመራረጥ እንማራለን።

**የክለሳ ጥያቄዎች**

(1)ጌታ በተነሣ በስንተኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐረገ ?

(2)ሲያርግ ከእርሱ ጋ የነበሩትና ያዩት እነማን ናቸው?መላእክቱስ ምን አሉአቸው።

**ትምህርቱ**

- ጌታችን ከሞት ከተነሣ ከ40 ቀናት በኋላ፣ደቀዛሙርቱን በደብረዘይት ሰበሰባቸው።መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዘዛቸው። ኃይልና ጽናት እንደሚቀበሉም ነገራቸው።መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላም ለአሕዛብ ሁሉ ስለእርሱ እንዲያስተምሩ አዘዛቸው።እየባረካቸውም ዐረገ። ደመናም ሰወረችው ።
- ደቀመዛርቱ ክርስቶስ ካረገ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሠው በአንድነት እየጸለዩ ቆዩ።
- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ሌሎቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑም አብረው ነበሩ፡120 ያህሉም ነበር።
- ከዚያም ቅዱስ ጴጥሮስ ተነሥቶ ክርስቶስን በካደው በይሁዳ ምትክ ስለሚመረጠው ተናገረ።ይሁዳ ክርስቶን እንደካደውና ኃጢአቱ ወደ ሞት እንደመራውም አስረድቶ *"ስለዚህ ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል።"* አለ።
- ዮሴፍና ማትያስን አቁመው *"የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ.... የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው"* ብለው ጸለዩ እጣም ተጣጥለው ለማትያስ ወጣ፤ማትያስም ከ11ዱ ደቀመዛሙርት ጋር 12ኛ ሆኖ ተቆጠረ።
- ደቀመዛሙርቱም ጌታችን እንዳዘዛቸው በኢየሩሳሌም ቆዩ።ጌታችን ወደሰማይ ከዐረገ ከአሥር ቀናት በኋላም፣ መንፈስ ቅዱስ ሁሉም ተሰብስበው ሳሉ በእሳት አምሳል ወረደ።የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ - ኃይልና እና በብዙ ልሳን መናገርን ተቀበሉ።
- የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩና ከተለያዩ አካባቢዎች የተሠበሰቡ ብዙ ሕዝቦች ነበሩ። ነገር ግን ሁሉም የደቀመዛሙርቱን ንግግር በራሳቸው ቋንቋ ይሠሙ ነበር።
- ቅዱስ ጴጥሮስ ከሌሎች ሐዋርያት ጋር ሆኖ ስለ ክርስቶስ አስተማረ፣3000/ሦስት ሺ/ ያህል ሰዎችም በዚያችው ቀን በትምህርቱ አምነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።
- ለክርስቶስ ቤተሰቦች (ለደቀመዛሙርቱ) መንፈስቅዱስ የተላከበትና ደቀመዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ የተቀበሉበት ዕለት ጰንጠቆስጤ (ጴንጥኮስት) ይባላል።50ኛ ቀን ማለት ነው። ክርስቶስ በተነሳ በ50ኛው ቀን ይህ ተፈጽሞልና 50ኛ ተብሏል።

**የሙከራጥያቄዎች**

1.) ጌታችንን የከዳው ደቀመዛሙር------------ ይባላል።

(2.) የተተካው ሐዋርያ _______________ ይባላል።

(3.) በይሁዳ መተካት እንዳለበት የተናገረው ______________ ነው።

(4) ለመተካት መጀመሪያ ____________________ አድርገው። ከዚያ በ______________ ለዩ።

(5) ሐዋርያት ጌታችን በተነሣ በ________ ቀን መንፈስቅዱስን ተቀበሉ።

**ይቆየን።**